# እያንጓለለ

ባቋሙ ያልጸና ፤ ልቡ እየዋለለ

በትግሉ ሳይቆርጥ ፤ የተቀላቀለ

ተንሸራቶ ጠፋ ፤ ቢፈለግ የት አለ?

ትግሉ እየጠራ ነው ፤ እያንጓለለ ።

ሀሞቱ የከዳው ፤ ሆድ ሆዱ የባባ

ተንደርድሮ ሄዶ ፤ ለወያኔ ይገባ

እያንጓለለ ፤ ፍሬን ከገለባ

ትግሉ እየጠራ ነው ፤ እንበል ጀባ ጀባ

መድረኩ ይጠራል ፤ መስከረም ሲጠባ ።

ያልቆረጠላቸው ፤ ወያኔን ቢያፈቅሩ

ትግሉ እየጠራ ነው ፤ ምንድነው ችግሩ

ቢያሻም በወረንጦ ፤ ለቅሞ  እያበጠሩ

እያንጓለሉ ፤ አረሙን ከዘሩ

መሸኘት ብቻ ነው ፤ ወደየመንደሩ ።

የነቀዘ ለዘር ፤ ሲሆን አልተሰምቶ

ፍሬም እያፈራ ፤ አልሰማን አልታይቶ

ተለቅሞ ይጣላል ፤ እያውቅም ተበልቶ

ለይቶ ጠራርጎ ፤ ባንድ ቅርጫት ሞልቶ

ይጥሉታል እንጂ ፤ ከቆሻሻ ደፍቶ

እያንጓለሉ ፤ ከጥሩው ለይቶ ።

ታዛቢው

November 23/2009